# ምዕራፍ ስድስት

## ተውኔት

**የምዕራፉ ዓላማዎች:- ተማሪዎች! ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፣**

- የተውኔትን ምንነት ትናገራላችሁ::
- የተውኔት አላባውያንን ትዘረዝራላችሁ::
- የአንድን ተውኔት ታሪክ በድርጊትና በጊዜ ቅደም ተከተል ታቀርባላችሁ::
- ውይይት ታካሄዳላችሁ::
- በምትጽፉት ጽሑፍ ውስጥ መሸጋገሪያና አያያዥ ቃላትን ትጠቀማላችሁ::
- ከቃላት ውስጥ የመነሻና የመድረሻ ቅጥያዎችን ትለያላችሁ::
- ቃላትን እንደ ባለቤት፣ ተሳቢና ማሰሪያ አንቀጽ ተጠቅማችሁ ዓረፍተነገር ትመሰርታላችሁ::
- በቃላት ላይ የተቀጠሉ የእርባታ ቅጥያዎችን ታመለክታላችሁ::
- ማመልከቻ ትጽፋላችሁ::
- ለዋጭ፣አነፃፃሪና ሰውኛ ዘይቤዎችን ለይታችሁ ታሳያላችሁ::

© MoE, FDR
Not to be rep

## ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

፩. ተውኔት ምንድነው?

፪. ካነበባችኋቸው የልቦለድ መጻሕፍት ውስጥ የምታስታውሷቸውን ገጸ-ባህርያት ጥቀሱ።

፫. በሬዲዮ እና በቴሌቪዥን እንዲሁም በመድረክ ቀርበው ከተከታተላችኋቸው ተውኔቶች ውስጥ የምታስታውሷቸዉን ገጸ-ባህሪያት ዘርዝሩና ገፀባህርያቱን ለምን እንደምታስታውሷቸው ግለጹ።

፬. ገጸ-ባህርያት ማለት ምን ማለት ነው? መቼትስ?

፭. ስለተውኔታዊ ቃላት የምታውቁትን ጥቀሱ።

## የተውኔት አላባውያን

የተውኔት አላባውያን ገጸ-ባህርያት፣ ታሪክ፣ መቼት፣ ትልም (ምክንያትና ውጤት) እና ግጭት ናቸው። እነዚህ የተውኔት አላባውያን በአንድ ተውኔት ውስጥ በተለያዩ መንገዶች ሊገለጹ ይችላሉ። በሚከተለው ተውኔት ውስጥ የተውኔት አላባውያን የሚባሉት በክዋኔ ይገለጻሉ።

### ትእይንት አንድ

(በመጀመሪያው ትእይንት መድረኩ ሲከፈት፣ ከብቶች ሳር እየጋጡ የሚስተዋሉበት መስክ ይታያል። ከብቶች ሳር እየጋጡ በሚታዩበት ፊት ለፊት ባለው አንድ ዛፍ ስር ሁለት ሰዎች ተቀምጠዋል። ከሁለቱ ሰዎች አንደኛው በራሳቸው ላይ ነጭ ሻሽ ጠምጥመዋል። ጋቢ ለብሰው በሚታዩት ሁለተኛው ሰው ትከሻ ላይ በአንደኛው ጫፍ መሬት የነካ ብትር ተጋድሟል)።

**ቄስ ታምሩ:-** «ብርቱ ጉዳይ አለኝ እፈልግዎታለሁ» ካሉኝ ሰነበቱ አይደል አያ ቦጋለ?



© MoE, FDRE Ethiopia Not to be republished

© MoE, FDRE Ethiopia Not to be republished

***አያ ቦጋስ:-*** «አዎ! ሰንበት ብሏል፤ እስካሁን ከቆየሁት አይበልጥም፤ እታገሳቸዋለሁ፤ ፋታ የማይሰጥ ጉዳይ አጋጥሟቸው ይሆናል» ብዬ ነው፡፡

***ቄስ ታምሩ:-*** አይ የኔ ነገር! አንዳንዴ እዘነጋለሁ፤ አንዳንዴ ደግሞ እርስዎም እንደሚያውቁት የንሰሐ ልጆቼ ከዚያም ከዚህም ይጠሩኛል፡፡ አሁን ዛሬ ትዝ ሲለኝ ጊዜ «አያ ቦጋለን ከብቶች የሚያግዱበት ቦታ አላጣቸውም» ብዬ ነው ደንግጬ የመጣሁት፤ ለመሆኑ የፈለጉኝ በደህና ኖሯል?

***አያ ቦጋስ:-*** ደህናስ ደህና ነኝ፤ እንዲያው ብቸኝነት ሲከብደኝ ጊዜ “ለምን አንድ ውሃ አጣጬን አልፈልግም” የሚል ሀሳብ ከታየኝ ሰንበት ብሏል፡፡

***ቄስ ታምሩ:-*** የማንን ልጅ አሰቡ? የትኛዋን ልጃገረድ አዩ?

***አያ ቦጋስ:-*** ኧረ እንዲያም አይደል፤ በዚህ እድሜዬ የማንንም ልጅ ለጋብቻ መጠየቅ አልሻም፡፡

***ቄስ ታምሩ:-*** ታዲያ በየትኛዋ ፊት ላይ ነው ቀልብዎ ያረፈዉ?

***አያ ቦጋስ:-*** ኧረ ሩቅም አይደል የሄድኩት! ከዚሁ ከጎረቤቴ አንዲት ሴት አይቻለሁ፡፡

***ቄስ ታምሩ:-*** ማንን ነው ያዩት? እመት ውድነሽን ወይስ ሌላ ሴት?

***አያ ቦጋስ:-*** (እያቅማሙ…) እንዴት ባንዴ ደረሱባት! እንዴት ባንዴ አገኙኝ!

***ቄስ ታምሩ:-*** ነገሩ ጥሩ ነው፡፡ እመት ውድነሽ ባሎቿ በተራ ሞተውባት የለ!…

***አያ ቦጋስ:-*** አዎ! እሱንማ አውቃለሁ… ሀሳቤን በውስጤ ደብቄ ከርሜያለሁ፡፡ አሁን አሁን ብቻዬን ከምሆን ሰው ይሻለኛል፤ ከወዲህም ለቁንጅናዋ ምንም አይወጣላት! ሞት እንግዲህ ለሁሉም አይቀር፤ እጣ ፈንታችን አይደል! የአንድዬ ፈቃድም ከሆነ ዘር ማትረፍም ደግ ነው፡፡

**ቄስ ታምሩ:-** ነገሩማ ደግ ነው፤ ነገር ግን እመት ውድነሽ «ከእንግዲህ ትዳር አላስብም፤ የተቀረውን እድሜዬን ብቻዬን እገፋለሁ» ትላለች አሉ፡፡

**አያ ቦጋለ:-** እስዎን መፈለጌ ለዚህ አይደል! በአንድ በኩል የንስሐ ልጆዎ ናት፤ በሌላ በኩል ደግሞ የሀይማኖት አባት እንደመሆንዎ በአካባቢያችን ከእርሶ ቃል ማንም አይወጣም ብዬ ነው፡፡ እና ሀሳቤን ለእርስዎ ከነገርኩ ጭንቀቴ የቀለለኝ መሰለኝ፡፡ ውለው ሳያድሩ ይጠይቁልኝ፤ ይጠይቁልኝ ብቻም አይደለም፤ እሺ ያሰኙልኝ፡፡

**ቄስ ታምሩ:-** እስቲ እሱ ይጨመርበት! እኔማ እንደዚህ ላለ ጉዳይ ቀጠሮም አልሰጥ፤ ደግሞ እሺ ላሰኛት እሞክራለሁ፤ ከቃሌ የምትወጣ አትመስለኝም፡፡

**አያ ቦጋለ:-** ባዶ አፍዎን እንዲያው ዝም ብዬ... በደረቁ...

**ቄስ ታምሩ:-** እድሜ ይስጠን፤ ለወደፊት እንደርስበታለን፤ ደህና ይዋሉ አያ ቦጋለ፡፡

**አያ ቦጋለ:-** ደህና ይዋሉ፤ የምትልዎን ቶሎ ያድርሱኝ፡፡...

**የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች**

ቄስ ታምሩ ይሳካላቸው ይሆን?
«ይሳካላቸው ይሆናል» ወይም «አይሳካላቸውም» የምትሉ፣
ካነበባችሁት ውስጥ ማስረጃ በመጥቀስ አብራሩ::::

## ትእይንት ሁለት

(ትዕይንት ሁለት የሚፈጸመው በእመት ውድነሽ በጣሙ ቤት ውስጥ ነው፡፡ ጊዜው ምሽት ላይ ነው፡፡ በቤት ውስጥ እመት ውድነሽ ከንስሐ አባታቸው ከቄስ ታምሩ ጋር ሲነጋገሩ ይታያል)፡፡

**ቄስ ታምሩ:-** አያ ቦጋለን ያውቋቸው የለ? ቦጋለ መብራቱን?



© MoE, FDRE Not to be republished

***እመት ውድነሽ፡-*** አያ ቦጋለን እንዴት አጣዋለሁ? አንድ አካባቢ ሁነን!

***ቄስ ታምሩ፡-*** «አንድ ክቡር ሃሳብ አለኝ» ይላሉ አያ ቦጋለ!

***እመት ውድነሽ፡-*** ምንድር ነው ክቡር ሃሳብ ደግሞ በአንድ አካባቢ እየኖርን?

***ቄስ ታምሩ፡-*** አያ ቦጋለ እስዎን «ለጋብቻ አስቤያታለሁ» ይላሉ፡፡

***እመት ውድነሽ፡-*** (እንደማፈርም እንደ ማዘንም ብለው፣ ቄስ ታምሩንም ለማየት አፈር እያሉ፣ ዓይናቸውን መሬት ላይ ተክለው ዝም ይላሉ፡፡)

***ቄስ ታምሩ፡-*** ወይዘሮ ውድነሽ! የከነከነዎ ነገር ምንድነው?

***እመት ውድነሽ፡-*** (ትንሽ እንደማፈርም እያሉ፣ አፋቸውም እየተሳሰረባቸው እንደምንም ብለው ራሳቸውን እያጠናከሩ) አያ ቦጋለ ሦስት ባሎች በተራ ካገባሁኝ በኋላ ሦስቱም በተራ እንደሞቱብኝ እዚሁ በአካባቢው ተቀምጦ እያወቀ እኔን «ላግባ» ብሎ መጠየቁ ማዘኔን ስለተረዳ፣ "ደስ ላሰኛት፣ ልጽደቅባት" ብሎ ነው? ወይስ... ምንድ ነው?

***ቄስ ታምሩ፡-*** (መልስ ለመስጠት ፈጠን እያሉ) የለም! የለም! እንደዚያ አይደለም፤ "ደስ አሰኝቻት ደስ ታሰኘኛለች" ብለው ነው እንጂ "ልጽደቅባት" ብለው አይደለም፡፡

***እመት ውድነሽ፡-*** (በመገረም ይጠይቃሉ) እንዴት!?

***ቄስ ታምሩ፡-*** *(ረጋ ደፈር በማለት መልስ ይሰጣሉ)* እስዎም ባሎችዎ በመሞታቸው ምክንያት፣ አያ ቦጋለም በልዩ ልዩ ምክንያት ብቸኝነት የሚያስከትለውን መከፋት ደኅና አድርጋችሁ ያወቃችሁ ስለሆናችሁ፣ ሁለታችሁ ብትገናኙ ተስማምታችሁ እንደምትኖሩ በማመን ነው፡፡ አያ ቦጋለ ቆዳቸው ሞኝ ቢመስል የዋዛ ሰው አይምሰሉዎ! ጥልቅ አሳቢ ናቸው፡፡

(እመት ውድነሽ የንስሐ አባታቸውን መልስ ከሰሙ በኋላ፣ አንገታቸውን ደፍተው ዝም ብለው ብቻቸውን የሆኑ በሚመስል

ካሳባቸው ጋር መሟገት ስለጀመሩ፣ ቄስ ታምሩ ይቀጥላሉ።) ይበሉ! እሺ ይበሉኝና አሳርጌ ልሂድ!

**_እመት ውድነሽ፡-_** (በዚህ ጊዜ፣ እመት ውድነሽ ሳንባቸው እስኪሞላ ጠለቅ አድርገው አየር ስበው በረዥሙ ይተነፍሱና) እሺ አባቴ እስዎ የመከሩኝን አልቀበልም ብዬ ወዴት እደርሳለሁ!? እሺ!

(እመት ውድነሽ የእሽታ መልስ ሰጥተው የንስሐ አባታቸውን ካሰናበቱ በኋላ፣ ስለ አያ ቦጋለ የሚከተለውን በሀሳባቸው ማመላለስ ይጀምራሉ። እመት ውድነሽ በሀሳባቸው ለራሳቸው ይናገራሉ።)

“አያ ቦጋለ መብራቱ መልከመልካም ነው፤ ነገር ግን ምንም ሀብት የለውም። እኔ ደግሞ የሞቱት ባሎቼ ሀብት አለኝ።”
(እመት ውድነሽ ከሀብታቸው በተጨማሪ መልካቸውም ለብዙ ሰዎች የሚደነቅ መሆኑን በማሰብ፣ ሙዳያቸውን ከጉሽጉሽ ላይ አውርደው ይዘው ይቀመጡና የመጨረሻ ባላቸውን ብላታ ብዙነህን ሲያገቡ የገዘዋትን ክብ መስተዋት አውጥተው ቦግ አድርገው ይከፍታሉ)።

በመስታዋቱ ውስጥ፣ አንዲት እንደመስተዋቱ ክብብ ያለች ፊት ከመስታዋቱ ውስጥ ብቅ ትላለች፤። እመት ውድነሽ መስታወቲቱን ትኩር ብለው ሲያዩዋት፣ እስዋም ትኩር ብላ ታያቸዋለች። አንገታቸውን ወደግራ ዘንበል አድርገው ወደመስታወቲቱ ቀረብ ሲሉ፣ እስዋም አንገትዋን ዘንበል አድርጋ ወደሳቸው ቀረብ ትላለች። እመት ውድነሽ ያቺን የምታምር ክብ ፊት እየተመለከቱ ለራሳቸው ይናገራሉ።

*(አዲስ አለማየሁ 1958፣ለማስተማሪያነት እንዲገለግል ሀሳብ ተጨምርበት የቀረበ)*

© MoE, FDRE Ethiopia
Not to be republished

© MoE, FDR
Not to be rep

## ክፍል አንድ:- ንባብ

**፩. ከተሰጡት አማራጭ መልሶች መካከል መርጣችሁ በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ:: ለምትሰጡት መልስ ማብራሪያ አቅርቡ::**

1. ጽሑፈ-ተውኔቱ ውስጥ የቀረቡት ቁስ ታምሩ፣ አያ ቦጋለ እና እመት ውድነሽ በስነ-ጽሑፍ ቋንቋ ምን ተብለው ይጠራሉ?

   ሀ) ግለሰቦች ሐ) ዋና ዋና ሰዎች

   ለ) ገጸባህርያት መ) ተዋንያን

2. በመጀመሪያው ትዕይንት ከሁለቱ ገጸባህርያት ጋር የሚታዩት ነገሮች ምንድን ናቸው?

   ሀ) ሰፊ መስክ

   ለ) ሳር የሚግጡ ከብቶች

   ሐ) በመስኩ ፊት ለፊት የሚታይ ዛፍ

   መ) የተጠቀሱት ሁሉ መልሶች ናቸው::

3. አያ ቦጋለ እመት ውድነሽ በጣሙን ለሚስትነት የፈለጉበት ምክንያት _______ስለሆኑ ነው?

   ሀ) ሀብታም ሐ) ቆንጆ

   ለ) አግብቶ ፈት መ) ብቸኛ

4. እመት ውድነሽ በጣሙ አያ ቦጋለን ለማግባት ያቅማሙት በምን ምክንያት ነው?

   ሀ) ቀደም ሲል ያገቧቸው ባሎች ስለሞቱባቸው፣

   ለ) ሀብት ስላልነበራቸው፣

   ሐ) ቆንጆ ስላልሆኑ፣

   መ) እድሜያቸው ገፍቶ ስለነበር

© MoE, FDRE Not to be reproduced

5. እመት ውድነሽ በመጨረሻ አያ ቦጋለን ለማግባት የተስማሙት እንዴት ነበር?
   ሀ) የንስሐ አባታቸው ግፊት ስላደረጉባቸው እንጂ እሳቸው አልፈለጉም።
   ለ) የቀደሙት ባሎቻቸው በመሞታቸው የሰዎችን አፍ ፈርተው እንጂ ውስጣቸው ደስተኛ ነበር።
   ሐ) አያ ቦጋለ መልከ መልካም እና ሀብታም ስለ ነበሩ በጋብቻው ውስጣቸው ተደስቷል።
   መ) አያ ቦጋለ መልከ መልካም አልነበሩም፤ ነገር ግን ሀብታም ስለነበሩ በልባቸው ተደስተዋል።
6. በጽሑፈ-ተውኔቱ የመጀመሪያ ትዕይንት ውስጥ የተገለፀው መቼት (መቼ? እና የት?) እንዴት ያለ ነው?
   ሀ) ምሽት፣አያ ቦጋለ ቤት፣
   ለ) ረፋድ ላይ፣መስክ፣ከብቶች ሳር የሚግጡበት ቦታ፣
   ሐ) ምሽት፣እመት ውድነሽ ቤት፣
   መ) ምሽት፣ቄስ ታምሩ መኖሪያ ቤት፣
7. በቀረበው ተውኔት ውስጥ የታየው ግጭት በምን ምክንያት የተፈጠረ ነው?
   ሀ) አያ ቦጋለ፣ እመት ውድነሽን ሲያገቡ የሚሞቱ መስሎ የታያቸው መሆኑ፣
   ለ) ለእመት ውድነሽ፣ በአከባቢያቸው የሚኖሩ ሰዎችን ሀሜታ መፍራታቸው፣
   ሐ) ቄስ ታምሩ፣ እመት ውድነሽ አያ ቦጋለን ለማግባት እንደማይፈልጉ መገመታቸው፣
   መ) እመት ውድነሽ፣ሀብታም ሰው ለማግባት ፍላጎት ያላቸው መሆኑ፣

8 በሁለተኛው ትዕይንት በተውኔቱ ውስጥ የተገለጸው መቼት በየትኛው ይገለጻል?

ሀ) ምሽት፣እመት ውድነሽ በጣሙ ቤት፣

ለ) ንጋት፣ እመት ውድነሽ በጣሙ ቤት

ሐ) ምሽት፣ ቄስ ታምሩ ቤት፣

መ) ንጋት፣ቄስ ታምሩ ቤት፣

9 በቀረበው ጽሑፈ-ተውኔት ውስጥ ምክንያትና ውጤት የተፈጠረው እንዴት ነው?

ሀ) እመት ውድነሽ በጣሙና አያ ቦጋለ መብራቱ ቢጋቡ ተረዳድተው መኖር መቻላቸው፣

ለ) እመት ውድነሽ በጣሙ አያ ቦጋለ መብራቱን ቢያገቡ አያ ቦጋለ መብራቱ የሚሞቱ መሆናቸው፣

ሐ) አያ ቦጋለ መብራቱ እመት ውድነሽ በጣሙን ቢያገቡ እመት ውድነሽ ሊሞቱ መቻላቸው፣

መ) አያ ቦጋለ መብራቱ እና እመት ውድነሽ በጣሙ ቢጋቡ ሁለቱም ሊሞቱ የሚችሉ መሆናቸው፣

**፪. ጥንድ ሆናችሁ በመወያየት የሚከተሉት ቃላት ወይም ሐረጎች በምንባቡ ውስጥ የገቡበትን ፍች ስጡ።**

| | |
|---|---|
| 1. ትዕይንት | 5. ተውኔት |
| 2. ሙዳይ | 6. የገሀድ ዓለም |
| 3. መድረክ | 7. አሳረገ |
| 4. ክዋኔ | 8. ውሃ አጣጪ |

**፫. የተዉኔቱን ዋና ዋና ድርጊቶች ቅደም ተከተላቸዉን ጠብቃችሁ ግለጹ፤ አሠራራችሁ በድርጊት አንድ በተገለጸው ምሳሌ መሠረት ይሁን፡፡**

**ድርጊት አንድ፣** አያ ቦጋለ፣ እመት ዉድነሽ በጣሙን ለማግባት ስለሚችሉበት ሁኔታ ከቄስ ታምሩ ጋር ተመካከሩ፡፡

**ድርጊት ሁለት፣**--------------------------------------------------

**ድርጊት ሦስት፣** --------------------------------------------------

**ድርጊት አራት፣**---------------------------------------------------

## ክፍል ሁለት፡- ንግግር

### የተውኔት አላባውያን

የተውኔት አላባውያን የሚባሉት ገጸባህርያት፣ ታሪክ፣ መቼት፣ ትልም (ምክንያትና ውጤት) እና ግጭት ናቸው፡፡

- ገጸባህርያት በአንድ ተውኔት ውስጥ በጸሐፊ-ተውኔቱ የሚፈጠሩ እና በተፈጠሩበት ተውኔት ውስጥ የሚያከናውኑት የሥራ ድርሻ ያላቸው፣ በገሀዱ ዓለም ሰውን መስለውና ሰውን ወክለው እንደ ሰው በመናገርና የተለያዩ ተግባራትን በመፈጸም የሚያገለግሉ ናቸው፡፡ ገጸባህርያት የሚናገርዋቸው ሆነ የሚፈጽሟቸው ድርጊቶች ለአንባቢያን ሆነ ለተመልካቾች ሙሉ በሙሉ ግልጽ ናቸው፡፡
- **መቼት**፡- ሌላ የተውኔት አላባ ነው፡፡ በአንድ ተውኔት ውስጥ ድርጊቱ መቼ እንደ ተፈጸመ፣ ጊዜውንና የት እንተፈጸመ ቦታውን ይገልጻል፡፡
- **ታሪክ**፡- በአንድ ተውኔት ውስጥ በንግግርም ሆነ በገጸባህርያት በድርጊት የሚከናወነው የአንድ ተውኔት ታሪክ ነው፡፡ የተውኔት ታሪክ ሌሎችን አላባውያን ይይዛል ማለት ነው፡፡ ገጸባህርያት፣ መቼት፣ ትልም እና ግጭት የሚፈጠሩት በአንድ ተውኔት ታሪክ ውስጥ ነው፡፤
- **ትልም**፡- ሌላው የተውኔት አላባ ነው፡፡ ገጸባህርያት የሚፈጽሟቸው ድርጊቶች ምክንያትና ውጤትን ተከትለው የሚካሄዱ እንደመሆናቸው፣ ትልም በተውኔቱ ውስጥ የሚካሄዱትን ነገሮች ምክንያትና ውጤት ያሳያል፡፡
- **ግጭት**፡- በአንድ ተውኔት ውስጥ የሚገኘው ሌላው አላባ ግጭት ነው፡፡ በአንድ ተውኔት ውስጥ ገጸባህርያት በሚያራምዱት ተግባር ወይም በሚያከናውኑት ታሪክ እርስበርሳቸው ወይም ይህን ላድርግ ወይስ አላድርግ በሚል በግል ከራሳቸው ጋር ይጋጫሉ፡፡ማንኛውም የተውኔት ታሪክ ያለግጭት ሊፈጠር አይችልም፡፡ ያለግጭት የሚፈጠር ታሪክ ተራ ታሪክ እንጂ የተውኔት ታሪክ አይሆንም፡፡



© MoE, FDRE Not to be reproduced

© MoE, FDRE Not to be reproduced

**፩. ቡድን በመመሥረት በትምህርት ቤታችሁ ወይንም በትምህርት ቤታችሁ አካባቢ ከሚገኝ ቤተመጻሕፍት ውስጥ፤ የተውኔት መጻሕፍትን በማንበብ፣**

1. አንድ የተውኔት ጽሑፍ ምረጡ።
2. የመረጣችሁትን የተውኔት ታሪክ ዋና ዋና ነጥቦችን ለይታችሁ መዝግቡ።
3. የተውኔት ታሪኩ ከምትኖሩበት የእውነታ ዓለም ጋር እንዴት ያለ ግንኙነት እንዳለው አጭር ማስታወሻ ጽፋችሁ ማብራሪያ ስጡ።

## ክፍል ሦስት፡- ጽሕፈት

**፩. ጥንድ ጥንድ በመሆን በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ ያሉትን ክፍት ቦታዎች ከቀረቡት አማራጮች መካከል መሸጋገሪያና አያያዥ ቃላት (ሐረጎች) የሆኑትን በመምረጥ አሟሉ።**

**በባዶ ቦታዎች ሊገቡ የሚችሉ መሸጋገርያና አያያዥ ቃላትና ሐረጎች**

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. በማስከተል | ለ. በመቀጠል | ሐ. ዳግመኛ |
| መ. በተደጋጋሚ | ሠ. ከዚህ ቀጥሎ | ረ. እስከዚህ ድረስ |
| ሰ. ከዚህ በማያያዝ | ሸ. ከዚህ በኋላ | ቀ. ታዲያ |
| በ. በሌላ ጊዜ | ተ. በዚህ አኳኋን | ቸ. ወደፊት |
| ኀ. ደግሞ | ነ. ብቻ | |

1. ተጋባዡ ተናጋሪ፣ መጻሕፍት የማንበብ ልምድን በሚመለከት ገለጻ አደረጉ፤ __________ ስለሚያነቧቸው መጻሕፍት በራስ አባባል ማስታወሻ መጻፍ ጠቃሚ እንደሆነ ተናገሩ።
2. የጤና ባለሞያው የኤች አይ ቪ ኤድስን የመተላለፊያ መንገዶች በሚመለከት ዋነኛ የሆኑትን በዝርዝር አቀረቡ፤ __________ በዚሁ ጉዳይ ላይም ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚያስፈልጋቸውን ነጥቦች ለይተው ገለጻ በመስጠት ንግግራቸውን ደመደሙ(ጨረሱ)።

3. ተውኔትን በሚመለከት ግጥሞችን አስፋፍቶ ተውኔቶችን እንዴት ማዘጋጀት እንደሚቻል ተምረናል፡፡ _______ አያያዥ ቃላትን ወይም ሐረጋትን እንማራለን፡፡
4. እስካሁን ያለው የንባብ ልምዳችን ብዙ የሚያኮራን ላይሆን ይችላል፤ _______ ግን አስፈላጊነቱን ስለተረዳን ጠንክረን ልናሻሽለው እንችላለን፡፡
5. ሁሉም ኢትዮጵያዊ የየድርሻውን በተሰማራበት ተግባር ለአገሩ እድገት ማበርከት አለበት፡፡ _______ የተሠሩት ሥራዎች በቂ ላይሆኑ ይችላሉ፡፡
6. እንደሌሎች ክበቦች ሁሉ በትምህርት ቤታችን የተውኔት ክበብ በሚገባ ተደራጅቷል፡፡ ክበቡ _______ በየሦስት ወራት የተለያዩ ተውኔቶችን ለተማሪዎች ያሳያል፡፡

**፪. በሚከተሉት አያያዥ ቃላት (ሐረጎች)፣ ዓረፍተነገሮችን መስርቱ፡፡ በመሠረታችኋቸዉ ዓረፍተነገሮች ውስጥ በተጠቀማችኋቸዉ አያያዦች ዙሪያ ሀሳብ ተለዋወጡና በሚሰጣችሁ ማሻሻያ መሠረት ዓረፍተነገሮቻችሁን እንደገና ጻፉ፡፡**

| |
|---|
| እና፣ ይሁን እንጂ፣ ሆኖም፣ ስለዚህ፣ ወይም፣ ነገር ግን፣ ከዚያም |

***ምሳሌ***፣ ሀ) በሕይወት ውስጥ የኑሮን ውጣ ውረድ መታገል እና ማሸነፍ ያስፈልጋል፡፡ (መታገልና ማሸነፍ የሚሉት ቃላት በ "እና" ተያይዘዋል)፡፡

ለ) ኃይሌ በብዙ ቦታዎች በሩጫ ስለ ተወዳደረ እና ስለ አሸነፈ ጥንካሬውን አረጋግጧል፡፡ (ስለተወዳደረ እና ስለአሸነፈ የሚሉት ሐረጎች በ"እና" ተያይዘዋል)፡፡

ሐ) የኤች አይ ቪ ኤድስ ሕመምተኛው ብቸኛ ነው፤ ስለዚህ በአጠገቡ ሆኖ የሚንከባከበው ሰው ያስፈልገዋል፡፡ (ሁለቱ ዓረፍተነገሮች በአያያዥ ቃል "ስለዚህ" ተያይዘዋል)፡፡

© MoE, FDRE Not to be reproduced

## የሥራ ደብዳቤ

ብዙ የደብዳቤ ዓይነቶች አሉ። ከነዚህ ዉስጥ አንዱ የሥራ ደብዳቤ ነው። የሥራ ደብዳቤ በተቋማት፣ በተለያዩ ድርጅቶች፣ በትምህርት ቤት ወዘተ. ውስጥ ለተለያዩ ክፍሎችና ለግለሰቦች ይጻፋል። የሥራ ደብዳቤ፣ የሚመለከተውን አካል ለማስታወስ፣ አንድ መሰረታዊ ጉዳይ ላይ ትኩረት እንዲደረግ ለማሳሰብና ትእዛዝ ለማስተላለፍ አገልግሎት ልይ ይዉላል። የሥራ ደብዳቤ ሲጻፍ የሚከተለውን ቅርጽ ይይዛል።

1. የሥራ ደብዳቤ የተጻፈለት ሰው ወይም ክፍል አድራሻ
2. የሥራ ደብዳቤውን የጻፈው ሰው ወይም ክፍል አድራሻ
3. የተጻፈበት ቀን
4. የተጻፈበት ጉዳይ
5. ዝርዝር ሐተታ
6. «ከሰላምታ ጋር» የሚለው ቃል እንደ መልካም ምኞት መግለጫ

© MoE, FDRE Ethiopia Not to be republished

ከዚህ ቀጥሎ የቀረበውን የሥራ ደብዳቤ ናሙና በአስተውሎት ተመልከቱ፡፡

ታህሳስ ፳፫ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም

ለመምህር ከበደ ታገል
የፀረ-ኤድስ ክበብ አስተባባሪ

ጉዳዩ፡- <u>በፀረ-ኤድስ ክበብ ተሳታፊ ያልሆኑትን የክበብ አባላት ስለማሳወቅ፣</u>

ጥቅምት ፰ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም የትምህርት ቤቱ የፀረ-ኤድስ ክበብ ሰብሳቢ ሆኜ መመረጤ ይታወሳል፤ ይሁን እንጂ፣ ሥራዬን ከጀመርኩበት ጊዜ አንስቶ አንዳንድ አባላት በምናደርገው ስብሰባና በምናከናውናቸው ተግባራት ላይ ፈጽሞ ተገኝተው አያውቁም፡፡ ከዚህ በፊት ይህንን ችግር በቃል ገልጬልዎት፣ በክበቡ ሥራ ውስጥ የማይሳተፉትን ተማሪዎች ስም ለይቼ በጽሁፍ እንዳቀርብልዎ መጠየቅዎ ይታወሳል፡፡ በመሆኑም የተማሪዎቹን ዝርዝር ከዚህ እንደሚከተለው አቅርቤያለሁ፡፡

1. ገመቹ ቱፋ
2. ተስፋዬ ጎይቶም
3. አየለች መታፈሪያ
4. ከድር ኡስማን
5. አስማማው ለገሰ

ከዚህ በላይ ስማቸው የተዘረዘረው ተማሪዎች በመደበኛ ስብሰባ ወቅትም ሆነ በሚደረገው የሥራ ክንውን ውስጥ አንድም ጊዜ ተገኝተው የማያውቁ መሆናቸውን በአክብሮት እገልጻለሁ፡፡

ከሰላምታ ጋር
ፊርማ
ከተማሪ መዝሙር ወርዶፋ
የትምህርት ቤቱ የፀረ-ኤድስ ክበብ ሰብሳቢ

© MoE, FDR
Not to be rep

፫. የቀረበላችሁን የሥራ ደብዳቤ በመከተል በትምህርት ቤታችሁ ውስጥ በሚገኙት ክበቦች ውስጥ በአንዱ ሰብሳቢ ሆናችሁ እንደተመረጣችሁ በመገመት የክበቡ አባል ሆነው አብዛኛውን ጊዜ ለማይገኙ ተማሪዎች የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ጻፉ፡፡

## ክፍል አራት፣ ሰዋስው

፩. የሚከተሉትን መነሻና መድረሻ ቅጥያዎች በመጠቀም ቃላትን መስርቱና ዓረፍተነገሮች ሥሩባቸው።

ምሳሌ፣ -ዎች፣ -ኦች፣ ሲ-፣ እየ-፣ ስለ-፣ በ-

፪. ቀጥሎ በቀረቡት ቃላት ዓረፍተነገር መሥርቱባቸው፤ ከዚያም በመሰረታችሁት ዓረፍተነገር ውስጥ የቃላቱን ሙያ "ባለቤትነት፣ ተሳቢነት" እያላችሁ ግለጹ፡፡

ምሳሌ፣ወጣቱ <u>ትውልድ</u> ሀገር ተረካቢ ነው፡፡

በዚህ ዓረፍተነገር ‹‹ትውልድ›› የሚለው ቃል ሙያ ባለቤትነት ነው፡፡

1. ትውልድ
2. ግንባታ
3. የእጅ ኳስ
4. መንቀፍ
5. ማህበር
6. ልማት
7. ሥነ ምግባር
8. አታላይ

፫. የሚከተሉትን ቃላት በነፃና በጥገኛ ምዕላድ ከፋፍሉ፤ ሙከራችሁንም ለክፍል ጓደኞቻችሁ በማቅረብ ተነጋገሩባቸው፡፡

ምሳሌ፣ሰዎች፤ ሰው-ኦች

ነፃ ምዕላድ ← ሰው-ኦች → ጥገኛ ምዕላድ

1. ገበሬዎች
2. ወንድሟ
3. ስሙ
4. በናትህ
5. ባርኔጣዎች
6. አገሯ
7. ገንዘቧ
8. ደብተርሽ
9. ቤቶች
10. አምራቾች

፬. በቡድን ሆናችሁ የራሳችሁን ነፃ እና ጥገኛ ምዕላድ የያዙ አምስት ቃላት በመፈለግ በቃሎቹ ውስጥ ነፃና ጥገኛ ምዕላዶችን ለዩና መልሳችሁ ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡና ተነጋገሩባቸው።

## ክፍል አምስት:- ስነጽሑፍ

፩. የሚከተለውን ግጥም (ልጅቱ የዘመነችቱ) ወደ ተውኔት ለውጣችሁ ካዘጋጃችሁ በኋላ፣ ክፍል ውስጥ መድረክ ላይ አቅርቡ። የተሻለ አቀራረብ አለዉ የምትሉትን ቡድን በጋራ ውይይት ምረጡ። (ከክፍል ውጭም በተለያዩ የትምህርት ቤቱ ክበባት መድረክ አዘጋጅታችሁ ተመልካች ባለበት ልትተውኑ ትችላላችሁ)። ግጥሙን ወደ ተውኔት በምትለውጡበት ጊዜ የሚከተሉትን በቅደም ተከተል አከናውኑ።

1. የቀረበውን ግጥም በሚያመቻችሁ መንገድ ማስፋት፣
2. ወደ ተሟላ ጽሑፈ-ተውኔት (የተውኔት ጽሑፍ) መለወጥ፣
3. ተውኔቱ የሚዘጋጅበትን መድረክ ማመቻቸት
4. በተውኔት ውስጥ በሚፈጠሩት ገጸ-ባህርያት መሠረት ተዋንያን /ተዋንያት/ መምረጥ
5. ለተውኔቱ አስፈላጊ የሆኑትን አልባሳት ማዘጋጀት፤
6. ተውኔቱን ማጥናት፣
7. ተውኔቱን መለማመድ
8. በልምምድ ላይ የሚታዩትን ስህተቶች ማረም፣
9. በመድረክ ላይ ማዘጋጀት እና የተመልካቾችን አስተያየት መቀበል

© MoE, FDRE Ethiopia Not to be republished

**የሚከተሉት ቃላት ቀጥሉ ከቀረበው ግጥም ውስጥ የወጡ ናቸው፡፡ ግጥሙን ወደ ተውኔት ከመለወጣችሁ በፊት፣ ግጥሙን ለመረዳት እንዲያግዛችሁ አገባባዊ ፍቻቸውን አስተውሉ፡፡**

1. ***የዘመነችቱ***፣ ዘመናይ መሆን፣ (በግጥሙ ውስጥ አጉል ሥልጣኔን የሚያመለክት ነው፡፡)
2. **ዳሩላዋን**፣ የታሰረ ፀጉሯን (ሴቶች በእንቅልፍ ሰዓት ፀጉራቸውን በወፍራሙ በሹሩባ ዓይነት ይቋጥሩትና ሻሽ ያስሩበታል፤ እንዳይበላሽ ለመጠበቅ ነው፡፡)
3. **ጥፍት**፣ መነካካት፣ (‹‹ጥ›› ይጠብቃል፤ በእጅ ጣቶች)
4. **ዱቅት**፣ ቅብት (‹‹ቅ›› የጥጠብቃል፤ መቀባት)
5. **ሱርት**፣ ልብስ (‹‹ብ›› ጠብቆ ይነባል፤ቃሉ ድርጊታዊ ቃል ነው፤ ሱሪ ከሚለው ቃል ነው የተመሠረተው፣ አለባበሷን ያመለክታል፡፡)
6. **ጭምት**፣ ጫማ ማድረግ፣መጫማት (‹‹ጭ››ይጠብቃል፤ ይህም ድርጊታዊ ቃል ነው፤ ጫማ ከሚለው ቃል ነው የተመሰረተው፣)
7. **ቀብትት**፣ እስር፣ አጥብቆ ማሰርን ያመለክታል፤ (በቃሉ መጨረሻ ላይ ያለው ‹‹ት›› ይጠብቃል፤ ይህም ቀበቶ ከሚለው ቃል የተመሰረተ ነው፡፡)
8. **ጅክት**፣ ልብስ (ይህም ቃል ጃኬት ከሚለው ቃል የተመሰረተ ድርጊታዊ ቃል ነው፡፡)
9. **ፕሮቫ**፣ የአለባበስ፣ የአጊያጊያጥ የአረማመድ ወዘተ. ልምምድ፤
10. **ገሪብ**፣ ያልሰለጠነ (በልጅቷ አስተሳሰብ ወላጆቿን ያልሰለጠኑ ናቸው ማለትዋ ነው፡፡)
11. **እያሳቀለች**፣ እየረገመች፣
12. **እየገረመመች**፣ በግልምጫ እየተመለከተች፣

© MoE, FDR Ethiopia Not to be republished

© MoE, FDR Ethiopia Not to be republished

## ወደ ተውኔት የሚለወጠው ግጥም

(ይህ ግጥም በምጸት የቀረበ ነዉ፡፡ ልጅቷ የሰለጠነች የሚመስላት፣ ነገር ግን ያልሰለጠነች፣ ጥራዝ ነጠቅ መሆንዋን ያመለክታል፡፡)

### ልጅቱ - የዘመነችቱ

**ልጅቱ - የዘመነችቱ**

ጧቱን ብድግ ንሥት
 ትለውና
ፊቷን ትጥብ እሽት
ፍትግ ፍትግትግ
ዳሩላዋን ልቅቅ ጥፍት
ሌላ ምናምን ዱቅት
ሽፋሏን ቅልም ጥቁርት
ከንፈርዋን ቅብት ቅልት
 ታደርግና፤

**ልጅቱ - የዘመነችቱ**

ሱሪዋን ለምበጫሙን - ሱርት
ጫማዋን ነጠላውን - ጭምት
ቀበቶዋን ሰፊውን - ቅብትት
ጃኬቷን የቆዳውን - ጅክት
 ታደርግና ፤

**ልጅቱ - የዘመነችቱ**

መስቷቱ - ትልቁ መስቷት ፊት
 ትቆምና፤
ሣቅ ግጥጥ … ሣቅ ግጥጥ … ሣቅ

ደርሶ ፍልቅ … ፍልቅልቅ … ፍልቅልቅልቅ
ከንፈር ገጠም … ደሞ ከፈት …
ደሞ ገጠም … ገጠምጠምጠም
ወደኋላ ሄድት … ሄድት
ደሞ ምልስ … ምልስ … ምልስልስልስ
ሽንጧን ሰበር … ቅልስ … ቅልስልስልስ
ዳሌዋን ውዝ ውዝ
ቂብ ቂብ … ቁንን ቁንን
ክው ክው … ጅንን ጅንን
ደሞ ፈገግ … ደሞ ቅጭም … ቅጭምጭምጭም
ዐይኗን ከፈት … ደሞ ጨፈን … ስልምልምልም
ደሞ ጉርጥ … ደሞ ጥቅስ … ደሞ ጉልጉል
(በራሷ ትቀልድ ይመስል)

ልጅቱ - የዘመነችቱ

ፕሮቫው ብሎ ጥቅልል
ወደ ቁርሷ መለስ ስትል
እማማዋ ንድድ ቁጥት
ትንሽ እህቷን ጥርት
በኩርኩም ግጭት!
"ገና ካሁኑ ይወጣብሽ
ለምነው ጧት መነሣትሽ?"
ደሞ ማለት፡፡
አባባዋም እዝን ቁጭት
ጸሎታቸውን ዝንግት
"ውይጉድ መበላሸት"
አርዝመው እያዩ ማለት፡፡



© MoE, FDR Ethiopia Not to be republished

**ልጅቱ - የዘመነችቱ**

ገሪብ ገሪብ እያለች
እማየዋን እያሣቀለች
አባዬዋን እየገረመመች
ቦርሳዋን እንደ ቦረሠች
ላስቲክ ብጤ ነገር ባፍዋ እያላመጠች
እያንቀጫቀጨች
ርፍድ ብሎባት ችኩል ችኩል እያለች
እሑድ ጧቱን ባንድ ሰዓት ውልቅ ያለች
(አፍታም ሳትቆይ - ወድያውኑ)
ሰኞ ጧቱን ምልስ ትላታለች።
ልጅቱ - የዘመነችቱ።

*(ደበበ ሰይፉ፣ 1980፣ 44 — 45)*

**፪. በሚከተለው ግጥም ውስጥ በሰውኛ ዘይቤ የቀረቡትን ክፍሎች ከለያችሁ በኋላ በግጥሙ ውስጥ የሚታየውን የሰውኛ ዘይቤ አጠቃቀም እና ባህርይ በማብራራት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።**

## ስደተኛው ዐባይ

ከኢትዮጵያ፣ ካፍሪቃውያን ገነት፤
በጐጃሙ ክፍል፣ ሰከላ ከሚሉት፤
ከዚያ ከረግረጉ፣ ከግሽ ዓባይ መሬት፤
ከዚያ ነው የፈለቅሁ፣ ዕወቁኝ ሊቃውንት።

ከዚያ ተነስቼ፣ ለመሄድ አቀድኩኝ፤
በኮረኮንች መንገድ፣ ጉዞየን ቀጠልሁኝ፤
በጥንተ ተፈጥሮ፣ እኔን የመሰሉኝ፤
በግራና በቀኝ፣ እክብረው አጀቡኝ፤
ትንሽ ወረድ እንዳልሁ "ወተት ዐባይ" አሉኝ።

ከዚያ ተነሥቼ፣ እየተዝናናሁኝ፤
በጣና ሐይቅ ላይ፣ አለፍኩና ሄድኩኝ፤
ከዚያ በኂላማ፣ ታላቅ ጅረት ሆንኩኝ።
ከዚያ አልፌ ስደርስ፣ ከታላቁ ቋጥኝ፤
ፏፏቴ ሆንሁና፣ ከሰማይ ወረድኩኝ።
ካጠገቤ ቁመው፣ የተመራመሩኝ፤
"ጢስ ዐባይ" አሉና፣ ሰሜን አወጡልኝ።

ጐጃምን ከጐንደር፣ እያካለልኩት፤
ወሎንም ከጐጃም እያዋሰንኩት፤
ሸዋንም ከጐጃም፣ እያካፈልኩት፣
ወለጋን ከጐጃም፣ እያካለልኩት፤
መንቀሳቀስ ጀመርሁ ወደተለምኩት።

*(ዜና ማርቆስ እንዳለው፣ 1992፣ 27-28)*

**፫. ከሚከተለው ግጥም ውስጥ አነጻጻሪ እና ለዋጭ ዘይቤዎችን ለዩና አጠቃቀማቸው እንዴት እንደሆነ በመግለጽ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርባችሁ ተነጋገሩባቸዉ።**

## ሙዚቃ

ፈልቀሽ የተገኘሽ፣ ከሹበርት ራስ፣
ከቤቶቨን ናላ፣ ከሞዛርት መንፈስ፤
ከሾፐን ትካዜ፣ ከያሬድ ልቦና፤
መዓዛ የሞላብሽ፣ የብስጭት ቃና፤
ረቂቋ ድምጽ ሆይ፣ ውቢቷ ሙዚቃ፤
ንጹሕ እንደ ፀሐይ፣ ውብ እንደጨረቃ።
የጨዋታሽ ለዛ፣ የድምጽሽ ፍስሐ፤
መሳይ ድንቅ  አረቄ፣ የነፍስ እህል ውሃ።
አገርሽ ገነት ነው፣ ስፈርሽም ኤደን፤



© MoE, FDRE Ethiopia Not to be republished

በሰማንሽ ቁጥር፣ ባሳብ መንገድ ሄደን፤
ታጫውቺናለሽ፣ በሕሊና ቋንቋ፤
ነፍሴ ካንቺ ጋራ፣ በመተዋወቋ፤
ትሽቆጠቆጣለች፣ ድምጽሽን ስትሰማ፤
ጠባይሽ ሲገለጥ፣ በምድራዊ ዜማ፤
መስሎ የሚመነጭ፣ ከገነት የወጣ፤
ጣዕሙ አይጠገብም፣ ቢጠጣ ቢጠጣ።
የትካዜ ከርቤ፣ የብስጭት ዕጣን፤
የመልአኮች ቋንቋ፣ የሱራፌል ልሳን፤
ቃናሽ ነፋስ ሆኖ፣ ድምጽሽ ሠረገላ፤
ውሰጃት እባክሽ፣ ነፍሴን ወደ ሌላ።

*(ከበደ ሚካኤል፣ 1994፣ 125)*

© MoE, FDR Ethiopia Not to be republished

© MoE, FDRE Ethiopia Not to be republished

## ማጠቃለያ

በምዕራፍ ስድስት ውስጥ የተውኔት አላባውያን ቀርበዋል፡፡ የተውኔት አላባ ውያን፣ገጸባህርያት፣ታሪክ፣መቼት፣ምክንያትና ውጤት፣ግጭት እና ጭብጥ ናቸው፡፡

ሐሳብን በጽሑፍ በመግለጽ ውስጥ የአጻጻፍ ሥርዓት አለ፡፡ በጽሑፍ የሚገለጽ አንድ ርዕሰ ጉዳይ በተለያዩ አንቀጾች ይገለጻል፡፡ ከአንድ አንቀጽ ወደ ሌላኛው አንቀጽ ለመሸጋገር አያያዥ ቃላትን መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

በንግግር እና በጽሑፍ በሚገለጹ ዓረፍተነገሮች ውስጥ የመነሻና የመድረሻ ቅጥያዎች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ እነዚህን ቅጥያዎች በትክክል መጠቀም የተፈለገውን ሀሳብ በንግግርም ሆነ በጽሑፍ ለሌላው ሳይሳሳት በሚገባ ለማስተላለፍና ለማድረስ ያግዛል፡፡

በንግግርም ሆነ በጽሑፍ በዓረፍተነገሮች አማካይነት የሚሸጋገሩትን ሀሳቦች ከስህተት የጸዱ እንዲሆኑ የመቆጣጠሪያው መንገድ በዓረፍተነገር ውስጥ በባለቤትነት፣ በተሳቢነትና በማሰሪያ አንቀጽነት የሚያገለግሉትን ቃሎች መለየት ይሆናል፡፡ እነዚህ ቃሎች መስተአምሮችን ሊያስከትሉ ይችላሉ፡፡

የሥራ ደብዳቤዎች በድርጅቶች፣ በመስሪያ ቤቶች፣ በትምህርት ቤቶች፣ በተለያዩ ተቋማት፣ ወዘተ. ለተለያዩ ክፍሎችና ግለሰቦች የሚጻፉ ደብዳቤዎች ናቸው፡፡ የሥራ ደብዳቤ የራሱ የሆነ የአቀራረብ ቅርጽ እንዳለው መረዳት ይገባል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. በቀረበው ጽሑፈ-ተውኔት፣ በትእይንት አንድና ሁለት ውስጥ ያሉት ገጸባህርያት ምን ዓይነት ድርጊት እንደሚፈጽሙ ለይታችሁ አመልክቱ።
2. ነፃ እና ጥገኛ ምዕላድ የያዙትን አምስት ቃላት በመምረጥ በነፃና በጥገኛ ምዕላዶች ከከፋፈላችሁ በኋላ ለነፃ እና ጥገኛ ምዕላድ መግለጫ በማዘጋጀት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።
3. በስም እና በግስ የቃል ክፍሎች ባለቤት ተሳቢና ማሰሪያ አንቀጽ ያላቸው አምስት ዓረፍተነገሮች ከመሰረታችሁ በኋላ በባለቤት በተሳቢና በማሰሪያ አንቀጽ ያገለገሉትን የቃል ክፍሎች በመለየት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡና ተነጋገሩባቸው።
4. በትምህርት ቤታችሁ ውስጥ ካሉት ክበባት በአንዱ፣ ሊቀመንበር እንደሆናችሁ ራሳችሁን በመቁጠር ክበቡ በሚያደርገው ስብሰባ ብዙ ጊዜ ለሚቀረው አንድ አባል የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ጻፉ።

© MoE, FDRE Ethiopia Not to be republished

© MoE, FDRE Not to be reproduced

# የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

፩. ከዚህ በታች በምዕራፍ ስድስት የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ሰንጠረዥ ቀርቧል:: በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ በነጥቦቹ ላይ በቂ ግንዛቤ ጨብጣችሁ ከሆነ /✓/ ምልክት አስቀምጡ:: ግንዛቤያችሁ አጠራጣሪ ከሆነ የጥያቄ ምልክት(?) አድርጉ:: ሙሉ ለሙሉ ግንዛቤ ከሌላችሁ /x/ ምልክት አስቀምጡ::

| ተ.ቁ | የማመሳከሪያ ነጥቦች | ✓ | ? | x |
|---|---|---|---|---|
| 1. | የተውኔትን ምንነት እና የተውኔት አሳባውያንን መግለጽ እችላለሁ:: | | | |
| 2. | የተወሰኑ ጽሑፈ-ተውኔቶችን አጥንቼ መጫወትና፣ መተወን እችላለሁ:: | | | |
| 3. | በምጽፈው ጽሑፍ ውስጥ መሸጋገሪያና አያያዥ ቃላትን በተገቢው ቦታቸው መጠቀም ችያለሁ:: | | | |
| 4. | ከቃላት ውስጥ መነሻና መድረሻ ቅጥያዎችን በመለየት አመለክታለሁ:: | | | |
| 5. | ቃላትን እንደባለቤት፣እንደተሳቢና እንደማሰሪያ አንቀጽ ተጠቅሜ ዓረፍተነገሮች እመሠርታለሁ:: | | | |
| 6. | የቃላትን ነፃና ጥገኛ ምዕላዶች ለይቼ አገልፃለሁ:: | | | |
| 7. | የተለያዩ የሥራ ደብዳቤዎችን መፃፍ እችላለሁ:: | | | |
| 8. | ከግጥሞች ውስጥ አነፃፃሪ፣ ለዋጭና ሰውኛ ዘይቤዎችን መለየት እችላለሁ:: | | | |
| 9. | የውይይትን ሥርዓት በመጠበቅ በተለያዩ ርዕሶች ዙሪያ መወያየት እችላለሁ:: | | | |

፪. ከዚህ በላይ በሰንጠረዡ የ(?) እና የ(x) ምልክቶች ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትረዷቸው ድረስ፣ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ::